# <u>ግዴታዊ የባዮሜትሪክ መታወቂያ - የማብራሪያ ጽሑፍ</u>

● የባዮሜትሪ የመረጃ ቋት (“ማአጋር”) ምንድን ነው? ይህ ኮምፒዩተራይዝድ የሆነና በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠበቅ የእያንዳንዱን ግለሰብ ልዩ መረጃዎች የያዘ የመረጃ ቋት ነው። የመረጃ ቋቱ የተቋቋመው በሕጉ መሠረት በመንግሥት አማካይነት ሲሆን የአገሪቱ ኗሪዎች የፊት ገጽታ ፎቶዎች ተጠብቀው ይያዙበታል። በመረጃ ቋቱ ውስጥ ስምምነታቸውን የሰጡ ሰዎች ሁለቱ የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎችም ይጠበቁበታል። የመረጃ ቋቱ በልዩ መሥሪያ ቤት አማካይነት የሚተዳደር ሲሆን ይህ የባዮሜትሪ የመረጃ ቋትን የሚያስተዳድረው መሥሪያ ቤት በሕዝብና ኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤት ሥር አይገኝም።

● **የባዮሜትሪ የመረጃ ቋት ተግባር ምንድን ነው?** የመረጃ ቋቱ ተግባር የፊት ገጽታ ፎቶዎችንና የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎችን ምርመራና ንጽጽር ማድረግ ሲሆን ይህም ማጭበርበርን ለመከላከል ይረዳል። ሌላው የመረጃ ቋቱ ዓላማ የመታወቂያ ስርቆትን ለመከላከልና አንድ ሰው አንድ መታወቂያ ብቻ እንዲኖረው ማድረግ ነው።

● **የባዮሜትሪክ መለያ መንገዶች**፡ የመታወቂያ ወረቀት፣ ፓስፖርት ወይም የይለፍ ወረቀት ለመቀበል በሚደረገው ሂደት ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ሁለቱ የአመልካች ጣቶች/ሌባ ጣቶች “ስካን” ተደርገው የሚወሰዱ ሲሆን የማመልከቻ አቅራቢው የፊት ገጽታም ፎቶግራፍ ይነሣል።

● **የባዮሜትሪ መለያዎችን ጠብቆ ማቆየት**፡
የባዮሜትሪ መለያዎች የሚጠበቁት፡
(ሀ) በመታወቂያው “ኤሌክትሮኒክ ቺፕ” ላይ የሁለቱ አመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራዎች ፎቶና የፊት ገጽታ ፎቶ ይጠበቃሉ።
(ለ) በባዮሜትሪው የመረጃ ቋት የሁሉም ኗሪዎች የፊት ገጽታ ፎቶዎችም ይጠበቃሉ።
(ሐ) በባዮሜትሪው የመረጃ ቋት ስምምነታቸውን የሰጡ ኗሪዎች የጣት አሻራዎችም ይጠበቃሉ።

የፊት ገጽታ ፎቶዎችንና የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎችን በኮምፒዩተር ጠብቆ ማቆየት በ“ኤሌክትሮኒክ ቺፕ”ና በመረጃ ቋቱ ውስጥ የሚገኙትን መረጃዎች ከአንድ ግለሰብ የፊት ገጽታ ፎቶና የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራዎች ፎቶ ጋር በማነጻጸር ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያስችላል። ይህም የሚፈጸመው የመለያዎችን ስርቆት ለመከላከል በሕጉ መሠረት ተደንግገው በወጡ መመሪያዎች ላይ ተመርኩዞ ነው።

● **ሁለት ፎቶዎችና የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች በመረጃ ቋቱ እንዲጠበቁ የሚደረግ ስምምነትና የመታወቂያ ወረቀቱና የፓስፖርቱ ተገቢነት ጊዜ**፡ በባዮሜትሪክ የመረጃ ቋቱ ውስጥ የሁለቱ አመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች እንዲጠበቁ የማስማማኗሪ (ይህም በግዴታ መልክ በመረጃ ቋቱ ከሚጠበቁ የፊት ገጽታ ፎቶዎች ተጨማሪ መሆኑ ነው)፣ እስከ 10 ዓመት

ድረስ የሚያገለግል መታወቂያና ፓስፖርት ይቀበላል። የጣት አሻራዎቹን ለማስቀመጥ የማይስማማ ግለሰብ ግን እስከ 5 ዓመት ድረስ የሚያገለግል መታወቂያና ፓስፖርት ይቀበላል።

የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች በባዮሜትሪክ የመረጃ ቋቱ ውስጥ እንዲጠበቁ መስማማት የግዴታ አይደለም። አንድ ኗሪ የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራዎቹ ተጠብቀው እንዲቆዩ የማይስማማ ከሆነ፣ አሻራዎቹ የንጽጽር ምርመራ ለማድረግ ወደ መረጃ ቋቱ የሚተላለፉ ሲሆን ምርመራው ካለቀ በኋላ ግን ከመረጃ ቋቱ ላይ ይፋቃሉ፣ በአጭሩ ተጠብቀው አይቆዩም።

● **የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች በመረጃ ቋቱ እንዲጠበቁ ስምምነት የሚሰጥበት መንገድ**

**ዓዋቂ፡** ሁለቱ የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች በባዮሜትሪክ የመረጃ ቋቱ ውስጥ እንዲጠበቁ ስምምነቱን የሚሰጠው በስምምነት ቅጹ ላይ በመፈረም ነው።

**18 ዓመት ያልሞላቸው ልጆች፡** የእነዚህ ልጆች (ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ ከሆነ ብቻ ነው) የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች በመረጃ ቋቱ ውስጥ እንዲጠበቅ የወላጆች ፊርማ ያስፈልጋል። ይህም ልጁ በስምምነት ቅጹ ላይ ከሚያሰፍረው ፊርማ በተጨማሪ ነው።

**ተንከባካቢ የተመደበለት ግለሰብ፡** የዚህ ግለሰብ የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች በመረጃ ቋቱ ውስጥ እንዲጠበቁ የተንከባካቢው ፊርማ ያስፈልጋል። እንክብካቤ የሚደረግለት ግለሰብ ደግሞ ጉዳዩን ከተረዳ እሱም በስምምነቱ ላይ ይፈርማል።

● ለ5 ዓመት የሚያገለግሉ መታወቂያ ወረቀቶች ወይም የጉዞ ሰነዶች (ፓስፖርት ወይም የይለፍ ወረቀት) የሚሰጡት አገልግሎት ለ10 ዓመት አገልግሎት ከተሰጡት ሰነዶች ጋር አንድ ዓይነት ነው። ይህም የሰነዱን የተገቢነት ጊዜ አይጨምርም።

● **18 ዓመት ላልሞላው ልጅ የሚሰጥ የጉዞ ሰነድ ተገቢነት ጊዜ** - ዕድሜው 18 ዓመት ላልሞላ ልጅ የሚሰጥ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት ወይም የይለፍ ወረቀት) የተገቢነት ጊዜ 5 ዓመት ነው።

● **የይለፍ ወረቀት (ለዓዋቂ ሆነ 18 ዓመት ላልሞላው ልጅ) ተገቢነት ጊዜ** - የይለፍ ወረቀት የተገቢነት ጊዜ 5 ዓመት ነው።

● **የሰጡትን ስምምነት በመሠረዝ በመረጃ ቋቱ ውስጥ ተጠብቀው የቆዩት የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች እንዲፋቁ መጠየቅ** - ከሴፕቴምቤር 1 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ በመረጃ ቋቱ ውስጥ ተጠብቀው የቆዩት የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች እንዲፋቁ ለሕዝብና ኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል። 18 ዓመት ያልሞላው ልጅ ወይም ተንከባካቢ የተመደበለት ግለሰብ የሰጡት የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች እንዲፋቁ ማመልከቻ ሲቀርብ ሁለት ጊዜ መፈረም አያስፈልግም። 18 ዓመት ያልሞላው ልጅ ወይም ተንከባካቢ የተመደበለት ግለሰብ ፊርማ ወይም የእነሱ ተወካይ ፊርማ በቂ ነው። በመረጃ ቋቱ ውስጥ ተጠብቀው የቆዩት የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች እንዲፋቁ ለሕዝብና

ኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤት ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ መታወቂያውን፣ ፓስፖርቱን ወይም የይለፍ ወረቀቱን መመለስ ያስፈልጋል። እነሱም ይሰረዙና በእነሱ ምትክ አዲስ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም የይለፍ ወረቀት የሚሰጡ ሲሆን የሚያገለግሉት ለ5 ዓመት ነው። እነዚህ አዳዲስ ሰነዶችን ለመቀበል እንደገና አዲስ ማመልከቻ ማስገባት ያስፈልጋል።

- **ጊዜያዊ ደንብ** - የአመልካች/ሌባ ጣቶች አሻራ ፎቶዎች በባዮሜትሪኩ መረጃ ቋት ውስጥ እንዲጠበቅ የሚሰጠው ስምምነት ጊዜያዊና ለ5 ዓመት ብቻ የሚቆይ ሲሆን በሕጉ መሠረት እንደገና ማራዘም ይቻላል።

- **የጣት አሻራዎችን በመረጃ ቋት ጠቆ የማቆየትና የመጠቀም አንድምታ - መረጃዎችን ለፖሊስና ለመከላከያ ባለሥልጣን ማስተላለፍ** - በሕጉ መሠረት አንድ ግለሰብ አሻራዎቹ በመረጃ ቋቱ ውስጥ እንዲጨምሩ ከተስማማ ፖሊስና የመከላከያ ባለሥልጣን፣ (የአገር ውስጥ ደኅንነት/“ሻባክ” እና “ሞሳድ”)፣ በሕጉ በተደነገጉ ጥቂት ቅድመሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ፣ ከመረጃ ቋቱ መረጃዎችን (የመለያ ውጤቶችን ወይም በመረጃውቋት ውስጥ የተቀመጡየፊት ገጽታ ፎቶዎችንና የጣት አሻራዎችን) መቀበል ይችላሉ። በመረጃውቋት ውስጥ የተቀመጡየፊት ገጽታ ፎቶዎችንና የጣት አሻራዎችን በሕጉ ከተደነገገው ውጪ መጠቀም **ክልክል** ነው።